የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፷
አዲስ አበባ–ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 60
ADDIS ABABA-22th May, 2003

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፵/፲፱፻፺፭ ዓ/ም

ለሐረር ከተማ የንፁህ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመ የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ........................ ገጽ ፪ሺ፩፻፹፰

## CONTENTS

Proclamation No.340/2003.

The African Development Fund loan Agreement for Financing the Harar Water Supply and Sanitation project Ratification Proclamation ......... Page 2188

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፵/፲፱፻፺፭

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለሐረር ከተማ የንፁህ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ፲፱ ሚሊዮን ፰፻፺ ሺ ዩ.ኤ. (አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና ሺ ዩኒትስ አፍ አካውንት) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፰ ቀን ፪ሺ፪ በአቢጃን የተፈረመ በመሆኑ ፤

መሠረታዊ የኢኮኖሚ ዓለም አቀፍ ውሎች ተፈፃሚ ከመሆናቸው በፊት መጽደቅ ስለአለባቸው ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ–መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ፤

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለሐረር ከተማ የንፁህ ውሃ አቅርቦት ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ብድር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፵/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪. <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክሪሲያዊ ሪፐብሊክ እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.ኤ.አ. ኖቬምበር ፰ ቀን ፪ሺ፪ በአቢጃን ኮትዲቫር ከተማ የተፈረመው ቁጥር ፪ ትሪሊዮን ፩፻ ቢሊዮን ፩፻፶ ሚሊዮን ፮ ሺ ፱፻፵፪ የብድር ስምምነት ነው ።

## PROCLAMATION 340/2003

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement between The Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Bank stipulating that the African Development Bank provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan Amount of U.A. 19,890,000 (Nineteen Million Eight Hundred Ninety Thousand Units of Account) for financing the Harar Water Supply and Sanitation Project was signed in Abidjan, on the 8th day of November, 2002;

WHEREAS, basic economic international agreements have to be ratified prior to enter in to force;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 22nd day of May, 2003;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub–Article (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as "The African Development Fund Loan Agreement for Financing the Harar Water Supply and Sanitation Project Ratification proclamation No. 340/2003"

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 2,100,150,006,942 signed on the 8th day of November, 2002; between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫. <u>የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፱ ሚሊዮን ፰፻፺ ሺ ዩ.ኤ (አሥራ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት መቶ ዘጠና ሺ ዩኒትስ ኦፍ አካውንት) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል። ።

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Power of the Minister of Finance and Economic Development*

The Minister of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan Amount of U.A. 19,890,000 (nineteen million eight hundred ninety thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force on the 22nd day of May, 2003.

Done at Addis Ababa this 22nd day of May, 2003.

GIRMA WOLDE GIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE